# ስልቻን ፤ ቀልቀሎ

ቀበሮ ፤ በግ ሲፈጅ ፤ እንሻረው ተብሎ
እረኛ ፤ እንዲሆን ፤ ተኩላ ተመልምሎ
አስቀያሚ ፊቱን ፤ አሳምሮ ስሎ
መልካም ምኞት ፤ ያለው ፤ ቅዱስ አመስሎ
መሰሉን ለመሾም ፤ ቀበሮን ፈንግሎ
በተኩላ መኩራራት ፤ ማን ከማን ፤ ተሸሎ ?
አልሸሹም ፤ ዞር አሉ ፤ ስልቻን ቀልቀሎ ።

ስልቻን ቀልቀሎ ፤ ቀልቀሎን ስልቻ
ፊታውራሪ ሆኖ ፤ ሻቢያ ፤ እንደ ጡንቻ
ባባቱ ትከሻ ፤ ልጁ ላይ ፤ ዘመቻ
ተኩላን ፤ ተገን ሆኖ ፤ ቀበሮ ላይ ፤ ዛቻ
አንድ አይነት ፤ ፈረስ ነው ፤ ቢቀየር ኮርቻ
አይጣፍጥም ወጡም ፤ ቀይሮ ጉልቻ
ሻቢያም ወያኔ ፤ የስም ፤ ለውጥ ብቻ ።

አባትና ልጁን ፤ እናውቅ ፤ የለም እንዴ !
ልጅየው ፤ ቂጥኛም ፤ አባቱ ነው ፤ ውርዴ
ስልቻን ቀልቀሎ ፤ ቀልቀሎን ስልቻ ፤ አትበሉን ከንግዴ !
በሽታው በልቷቸው ፤ ዛሬ ፤ ሲሉ ዳዴ
ሰንኮፉን ፤ መንቀል ነው ፤ ማስወገድ በዘዴ
ስልቻም ቀልቀሎ ፤ቀልቀሎም ወንበዴ
እንዳያንሰራሩ ፤ መጥረግ ፤ ሁሉን አንዴ ።

ታዛቢው

February, 24, 2010